**CUDE LAUNCH RADIO PROGRAM**

**TRAINING AND CONSULTANCY DIVISION ORGANIZES LIFE SKILL TRAINING FOR THE CONSULTANTS**


# Ethiopian CIVIL SERVICE University

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ

ECSU

Monthly Newsletter Vol 15 No. 7

JAN, 2019




## ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY
### PARTICIPATES IN 8TH ETHIOPIAN URBAN FORUM




**ባለፈው ክረምት ባደረግነው ቆጠራ በቤተ መጽሐፉ ሰላሳ አምስት ሺ የሚሆን የመጽሐፍ ክምችት መኖሩን አረጋግጠናል፡፡**

**አመለወርቅ ውቤ**

የ ቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## እሴቶቻችን

- ተገልጋይ ተኮር
- ቁርጠኝነት
- ሁሌም መማር
- ብዝሀነት መቀበል
- ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
- አሳታፊነት
- ተባብሮ መስራት

## Our Values

- Customer Focus
- Commitment
- Continuous Learning
- Welcoming Diversity
- Attention to the Disadvantaged
- Participation
- Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY PARTICIPATES IN 8TH ETHIOPIAN URBAN FORUM — 1

CUDE LAUNCH RADIO PROGRAM — 2

TRAINING AND CONSULTANCY DIVISION ORGANIZES LIFE SKILL TRAINING FOR THE CONSULTANTS — 3

ECSU COMMUNITY DONATES TO WOREDA 11 WOMEN AND CHILDREN'S AFFAIRS OFFICE — 5

ቅኝት በቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት — 6

የአረንጓዴ ክለብ ምስረታ በኢ.ሲ.ሰ.ዩ — 9



**Editor In -Chife**
Wondimu Moges

**Editors**
Wondimu Moges
Seifu Bekuretsion
Tariku Ayano
Anteneh Demisse

**Photos**
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

**ግራፊክስ Design**
Dereje Tesfaye



ECSU

International & Public Relations Directorate

Tel.0116462887
0116463015
E-mail;IPRD@ecsu.edu.et/
pr.ecsu@gmail.com

Po.box 5648
website;www.ecsu.edu.et
FM RADIO 100.5 MHz

# ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY PARTICIPATES IN 8TH ETHIOPIAN URBAN FORUM

Ethiopian Civil Service University participated in 8th Ethiopian Urban Forum which was held from February 15- 21/2019 in Somali Regional State capital Jigjiga. In the forum, more than 150 cities participated. The University was given a place in a pavilion rented by Addis Ababa City Administration and able to display models of urban design and other important statistical information in banners and pictures. Visitors applaud the Universities efforts to support the urbanization efforts in the country.



In the occasion his Excellency Mustefa Mohammed, Vice president of Somali Regional State and Ato Kassahun Goffe, State Minister of Ministry of Urban Development and Construction visited the exhibition and the University`s team explained the programs, success and future plans of the University and what the university is doing through College of Urban Development and Engineering and Urban Development Training Center.











In parallel events in the forum, the University`s professors presented two research papers: "The effects of Public Service Tools Implementation on the Quality of the Public Service delivery", by Dr.Merga Mekuria and Dr. Degu Bekele, and "Assessment of Provision for Economic Empowerment of Women" by Dr. Alemayehu Debebe. The presentations were moderated by Ato Jantirar Abay Minister of Urban Development and Construction and Ato Bezabih Petros, Commissioner for Civil Service Commission and Ato Tazer Gebre Egziabher State Minister of Urban Development and Construction respectively.

Commissioner Bezabih in the occasion said, "Had it not been for Ethiopian Civil service University`s interventions, the urbanization efforts in the country would have failed. We need to acknowledge the university`s contribution." Ato Tazir also said that the ongoing cooperation between the Ministry of Urban Development and Construction and the University would be intensified hinting on upcoming collaboration agreements. The participants also urged the University to exert efforts and be champion in urban development in the country.











# CUDE LAUNCH RADIO PROGRAM

Ethiopian Civil Service University College of Urban Development and Engineering (CUDE) officially launched a radio program that focuses on environmental issues on Ethiopian Civil Service University Community Radio FM 100.5 on February 1, 2019 on the event held at FM100.5 radio station. The program entitled "Our Environment" which has been organized and coordinated by Dr. Bisrat Kifle, CUDE vice dean.

On the launching program it was mentioned that CUDE, besides to its regular delivery of specialized educational program building the capacity of the public servants in area of urban engineering, is committed to support the ongoing effort exerted to alleviate environmental problems at national level. The program has with the objective of creating awareness on urban environment development to the ECSU community and its environment community in particular.





**Dr. Bisrat Kifle**
vice dean of CUDE

On the weekly radio program, major issues related to urban plan and development, environmental protection, climate change, urban infrastructure and transportation, urban land development, urban housing development urban engineering are going to be entertained and transmitted for the next six months.

The program will be coordinated by Dr. Bisrat Kifle vice dean of CUDE, and prepared and presented by Ato Mokonen Maschal and Ato Abel Zewdu from the Department of Environment and Climate Change Management.



# Training and Consultancy Division Organizes Life Skill Training for the Consultants

Ethiopian Civil Service University Training and Consultancy Division organized life skill training program from January 21-24 2019 at ECSU.

At the opening of the program, Dr. Waqgari Negari vice President for Training and Consultancy Division said that these Life skill trainings are the skills that a person must possess in order to successfully live in today's world. These include knowing how to work at a job and be part of a team, manage time, and live as part of family and learning effective communication skills. It is a program which can help us know each other very well. How effectively work at a job is a very important life skill for any employee in the organization he added.

According to Ato Daba Moti, Director for Consultancy Coordination Directorate the training was focused on the conceptual points on life skills and all consultants at the division participated in the training and they will be train of trainer.











# ECSU Community Donates to Woreda 11 Women and Children's Affairs Office

Ethiopian Civil Service University Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate made a donation program to Yeka sub-city Woreda 11 Women and Children's Affair Office to support HIV/AIDS positive children. On the donation program, organized as part of a community service, nine thousand seven hundred and thirty five birr and clothes collected from the university community were donated.







w/ro Abay Akemachew
Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate Director

According to w/ro Abay Akemachew, Gender and HIV/AIDS Prevention and Control Directorate Director, the objective of the donation program was to support and discharge the responsibility of the university community assisting HIV/AIDS positive children and lost their family in HIV/AIDS. "A permanent supporting program has been planned for the future. Until it becomes fully implemented such kind of donation program will continue .Besides, it is important that the university's communities should further strengthen their support", w/ro Abay noted.

The money and clothes collected from the university community were handed over to the Yeka sub-city Woreda 11 women and children affairs representative.

# ቅኝት በቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ ሰርቪሱን አቅም ለመገንባት የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እና ሰልጣኞችም ተፈላጊን እውቀትና ክህሎት ቀስመው እንዲወጡ ለማስቻል የትምህርት ፋሲሊቲዎች በበቂ ሁኔታ የማሟላት ተግባርን ቀዳሚ አጀንዳው አድርጎ በመስራት ላይ ይገኛል፡ ፡ በዚህ ረገድ ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው መካከል ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ቤተ መጻሕፍት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ቤተ መጻሕፍቱም ለተጠቃሚዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ በጥራትም በስፋትም እያሳደገ የመጣ ሲሆን በየጊዜው የሚያስመዘግበው ለውጥም የሚያበረታታ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እኛም በአጠቃላይ በቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በተመለከተ ከወ/ት አመለወርቅ ውቤ የ ቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆኖ ከልብ እናመሰግናለን፡፡***

**ወ/ት አመለወርቅ:-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- በመጀመሪያ እስቲ ራስዎን ያስዋውቁ፡፡***

**ወ/ት አመለወርቅ:-** ወ/ሮ አመለወርቅ ውቤ እባላለሁ፡፡ ቀደም ሲል በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ለአስር ዓመታት በኃላፊነት አገልግያለሁ፡ ፡ ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በዝውውር በመምጣት በቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርነት በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት የሚሰጣቸውን ዋና ዋና አገልግሎቶች ቢገልጹልን፡፡***

**ወ/ሮ አመለወርቅ:-** የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዋና ዓላማው የመማር ማስተማሩ ሂደትን በመረጃ መደገፍ ነው፡፡ በሚሰጣቸውም አገልግሎቶችም ግንኙነቱ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከተመራማሪዎች ጋር ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው 6540 የሚሆኑ ተማሪዎችና ወደ 311 የሚሆኑ የአካዳሚክ ስታፍ ሲኖሩ ተመራማሪዎችን ጨምሮ ለእነዚህ ሁሉ አካላት አገልግሎት እንሰጣለን፡ ፡ የምንሰጠውም አገልግሎት በሁለት ዘርፍ ተከፍሎ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህም የአንባብያን አገልግሎት ዘርፍና የቴክኒክ ዘርፍ ነው፡፡

በአንባብያን አገልግሎት ዘርፍ ሁለት ቤተ መጻሕፍት አሉ፡፡ እነዚህም ዋናው ቤተ መጻሕፍትና በከተማ ልማትና ምህንድስና ኮሌጅ የሚገኘው ቤተ መጻሕፍት ናቸው፡፡ በእነዚህ አብያተ መጻሕፍት በአገልግሎት ዘርፉ የመጻሕፍት ማጣቀሻ፣ ሰርኩሌሽን፣ የዶክመንቴሽን ፣ የኢንተርኔትና ለአካል ጉዳተኞችና ለዓይነ ስውራን የሚሰጥ ልዩ አገልግሎት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ ውጪ የመጻሕፍትግምጃቤትምአለን፡፡በቴክኒክዘርፍደግሞ የኦቶሜሽን፣የዲጂታል፣የካታሎግ፣ክላሲፊኬሽን የመሳሰሉት የቴክኒክ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

በእነዚህ ሁለት አደረጃጀቶች አማካይነት ቤተ መጻሕፍቱ በሳምንት ለሰባት ቀናት (ከብሔራዊ ክብረ በዓል ቀናት ውጪ) የሃያ አራት ሰዓት የንባብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የኢንተርኔት አገልግሎትም በኮምፒዩተር ክፍሎቻችን አልያም ተጠቃሚው የራሱን ላብቶፕ ኮምፒዩተሮችን ይዞ በመምጣት የኢንተርኔት አገልግሎት ከቤተ መጻህፍቱ ማግኘት ይችላል፡፡ የመረጃ ምንጮችን ማለትም መጻሕፍትን፣ ጆርናሎችንና የመሳሰሉትን ለተጠቃሚዎች የማዋስ አገልግሎትም እንሰጣለን፡፡ ይህም የማጣቀሻ መጻሕፍትን በማደራጀት እንዲሁም ቴሲሶችንና ዲሰርቴሽኖችን በማሰባሰብ ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች ጃውስ በሚባለው ሶፍት ዌር አማካይነት አገልግሎት እንዲያገኙም ይደረጋል፡፡ ቤተ መጽሐፉ የሚሰጠው ሌላው አገልግሎት ደግሞ የዲጂታል ላይብራሪ አገልግሎት ነው፡፡ በዚህ አገልግሎት አማካይነት በዩኒቨርሲቲው ያሉ አገልግሎት ፈላጊዎች በየትኛውም ስፍራ ሆነው የዲጂታል ላይብረሪ አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ ከተለያዩ አብያተ መጻሕፍት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ተገልጋዮች በዚህ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ የማያገኙት አገልግሎት ካለ እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና የመሳሰሉት ተቋማት ጋር ባለን ግንኙነት መሰረት አገልግሎት እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡

ከዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና ሰራተኞች በተጨማሪም ቤተ መጽሐፉ ለውጪ አንባብያንም የሚሰጠው አገልግሎት አለ። በአካባቢው ብዙም አብያተ መጻሕፍት ባለመኖራቸው በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በዚህ ቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ከፍተኛ ፍላጎት አለ። ካለው የቦታ ጥበት አንጻር የአካባቢው ማህበረሰብ የሚፈልገውን ያህል ባይሆንም ለተወሰኑት በተመጣጣኝ ክፍያ እንዲሁም የማስተርስና የፒኤ ዲ ተማሪ የሆኑትን ደግሞ ከሚማሩበት ተቋም ደብዳቤ እንዲያመጡ በማድረግ ያለ ምንም ክፍያ እናስተናግዳለን።

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፦ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቤተ መጻህፍቱ አንዳንድ አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎች እየተተገበሩ እንደሆነ ይገለጻል። እነዚህ የአሰራር ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑና ያስገኙትን ውጤት በዝርዝር ቢያስረዱን።***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፦** ከአንድ ዓመት በፊት ወደዚህ ዩኒቨርሲቲ ተዛውሬ እንደመጣሁ ወደስራው በቀጥታ ከመግባቴ በፊት በመጀመሪያ ያደረግነው ነገር ከቤተ መጻሕፍት ሰራተኞች ጋር ውይይት ማድረግ፣ መዛግብትን መመርመር እና በአካል የሚታዩ ክፍተቶችን የመለየት ስራን ነው ለሁለት ወራት ያህል ያደረግሁት። በመቀጠልም ከቅርብ የስራ ኃላፊዎች ጋር ስለችግሮቹ በመወያየት በአጭር ጊዜ ፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ዕቅድ የሚፈቱት ችግሮችን በመለየት ወደስራ ገብተናል ።

በአጭር ጊዜ ሊሰሩ ይገባል ብለን ከያዝናቸው ስራዎች መካከል የቤተ መጻሕፍቱን ህግና ደንብ በመከለስ አጸድቀን ተግባራዊ አድርገናል። በተማሪዎች የሚሰሩ ቴሲሶችና ዲዘርቴሽኖች የሚቀመጡት በሀርድ ኮፒ ስለነበር ወደ ሶፍት ኮፒ በመቀየር በዌብ ሳይት ላይ ገብቶ እንደ ዲጂታል ላይብረሪ ሁሉ በዩኒቨርሲቲው የተሰሩትን ስራዎች ሌሎች አካላት እንዲያገኙት ይደረጋል። ይህ ዩኒቨርሲቲው በሌሎች አካላት ሳይት እንዲደረግ ያደርጋል። በብዛት ሳይት መደረጉ ደግሞ የዩኒቨርሲቲውን ደረጃ ከፍ በማድረግ ተመራጭ ተቋም ያደርገዋል። በቅርቡ ለዩኒቨርሲቲዎች በተሰጠ ደረጃ ዩኒቨርሲቲው በዌብ ሳይት እና ዲጂታል ላይ ባለው መረጃ አማካይነት በኢትዮጵያ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች አስራ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡ ፡ ካለው የኢንተርኔት አቅም በመነሳት ከአንድ እስከ አምስት ባለው ደረጃ ውስጥ መግባት እንዳለበት ግን ይታመናል። ስለዚህ የአይአር ማስተርስ ቴሲስ እና ዲዘርቴሽን በብዛት ሳይት እንዲደረግ ለማስቻል የአይ አር ፖሊሲ እንዲጸድቅ ረቂቁን አዘጋጅተን ለሴኔት አቅርበናል።

ሌላው የመጽሐፍ ግዢ በየዓመቱ እንደሚፈጸም ይታወቃል። በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ የነበሩት መጻሕፍት ደግሞ በአብዛኛው ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ነበሩ። መረጃዎች ደግሞ በየጊዜው ይለዋወጣሉ። ይህን በመገንዘብ ለትምህርት ክፍሎች ደብዳቤ በመጻፍ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ አድርገን ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የመጻሕፍት ግዢ በሂደት ላይ ይገኛል። ቀደም ሲል ወደ ቤተ መጽሐፉ የሚገቡ መጽሔቶችና ጋዜጦችን በተመለከተም በተለያዩ አቅራቢዎች እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር ። ይህ ደግሞ ውል ለመዋዋል በራሱ አስቸጋሪ ነበር። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት አቅራቢዎች በጨረታ እንዲወዳደሩ ተደርጎ በአሁኑ ወቅት ከሁለት አቅራቢዎች ብቻ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን እንዲያቀርቡ ተደርጓል።




**ወ/ሮ አመለወርቅ ውቤ**
የ ቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የቤተ መጻሕፍቱን የሰው ኃይል መዋቅር በተመለከተም ቀደም ሲል የነበረው የቤተ መጻሕፍቱ የሰው ኃይል አደረጃጀት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት ፋላጊውን ሊያስተናግድ የሚችል መዋቅር አልነበረም ለማለት ይቻላል። በዚህም ላይ ጥናት አድርገን መስተካከል ያለበትን በመለየትና የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ በማካተት ጥናቱን አቅርበናል፡ ፡ በሰራተኞች በኩል የሚነሱ ቅሬታዎችን ለምሳሌ የትርፍ ሰዓት ክፍያና የመሳሰሉትን ለመፍታት ጥረት አድርገናል። ለሰራተኞች ስልጠናዎችን በመስጠትና የሚያነሷቸውን ጥያቄዎችም ከኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ክፍተቶችን ለመሙላት ጥረት ተደርጓል።በመካከለኛ ጊዜ ዕቅድ ለማሳካት ከታቀዱት ስራዎች መካከል አንዱ የቤተ መጻሕፍት ፋሲሊቲዎችን ማሟላት ነው። ተጠቃሚዎች የሚገለገሉባቸው እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ ወዘተ ያሉትን ማሟላት እንዲሁም ምቾቱንና ጸጥታውን ማስከበር ተገቢ ነው። በዚህ ረገድ የነበረው ሁኔታ

አርኪ ስላልነበር ለዩኒቨርሲቲው አመራር ሀሳብ አቅርበን አንድ ሚሊየን ብር የሚጠጋ በጀት ተመድቦልን ፋሲሊቲዎችን ለማሟላት በግዢ ሂደት ላይ እንገኛለን፡፡

ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ስራችን የዩኒቨርሲቲው ቤተ መጻሕፍት ባልታወቀ ምክንያት ለአስር ዓመታት ቆጠራ ሳይደረግበት ቆይቷል፡፡ ስለዚህ ለሰራተኞቻችን ለሁለት ቀናት ስልጠና በመስጠት ቆጠራ እንዲደረግ አድርገናል፡፡ ቆጠራውም ረጅም ጊዜ የወሰደና አድካሚ ነበር፡፡ በተደረገው ቆጠራ “ምን ያህል መጻሕፍት በቤተ መጻሕፍቱ ይገኛሉ? ምን ያህሉስ በግለሰቦች እጅ ናቸው? ምን ያህሉ አዳዲስ ናቸው? ምን ያህሉስ ከካታሎጋችን ጋር ይጣጣማሉ?” የሚለውን በመፈተሽ ማስተካከያ አድርገናል፡፡ የማስተካከል ስራውም ክረምቱን ሙሉ የወሰደ ነበር፡፡ ለአስር ዓመታት ያልተነካ ስራ ስለነበር አድካሚ ቢሆንም ሰራተኞቹ ጋር በነበረው የቁርጠኝነት ስሜት ስራውን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን ችለናል፡፡ በቆጠራ ወቅት ባደረግነው ስራም አንድ ክፍል ውስጥ ተከማችተው የነበሩና በርካታ ዓመታትን ያስቆጠሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች በጨረታ እንዲሸጡ አድርገናል፡፡ እነዚህ ጋዜጦችና መጽሔቶች ከአስር ዓመታት በላይ የሆናቸው በመሆናቸው መረጃዎችን ከነዚህ ጋዜጦችና መጽሔቶች የሚፈልግ አካል ከብሔራዊ ቤተ መዛግብት ማግኘት ስለሚችል ከአንድ ዓመት በላይ የሆናቸውን ጋዜጦችና መጽሔቶች ማከማቸቱ አስፈላጊ ባለመሆኑ በጨረታ እንሸጡ በማድረግ ክፍሉን እንዲለቁ ተደርጓል፤ ከዚህ በኋላም እስከ አንድ ዓመት የሆኑትን ብቻ ነው በመረጃነት የምንይዘው፡፡ ሌላው በሁለቱም አብያተ መጻሕፍት ላይ የፍሳሽ ችግር ነበር፡፡ ለጥገና ክፍል ጥያቄ በማቅረብ ለሁለቱም አብያተ መጻሕፍት ጥገና ተደርጎ ፍሳሹን በማስቆም ቀለም እንዲቀባ ተደርጓል፡፡

ቀደም ሲል ወደ ዲጂታል ላይብረሪ መጻሕፍትን የማስገባት ስራ ይሰራ እንደነበር ይታወቃል ፡፡ ነገር ግን ወደ ዲጂታሉ የሚገቡት መጻሕህት ዋጋቸው አይተመንም ነበር፡፡ ለዩኒቨርሲቲውም ምን ያህል እሴት እንደጨመረ አይታወቅም ፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓመት ምን ያህል መጻሕፍትን ወደ ዲጂታል ላይብረሪው እንዳስገባን በመለየት በዋጋ ሲተመኑ ምን እንደሚመስሉ ከአማዞን ላይ ዋጋቸው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ባለፈው ስድስት ወር በርዕስ 4811 ፤ በዋጋ ሲሰላ ደግሞ 4,664,913.63 ብር የሚያወጡ መጻሕፍት ተሰብስበው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ይህንም በስድስት ወር ሪፖርታችን ላይ አቅርበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከዚህ ሪፖርት ወዲህ ባለው የጥር ወር ብቻ በርዕስ 1076፤ በዋጋ ሲሰላ ደግሞ 3,172,477.47 ብር የሚያወጡ መጻሕፍት የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህንን ጨምሮ እስካሁን የተሰባሰቡት መጻሕፍት አጠቃላይ ዋጋ ሲተመን 7,837,390.38 ብር ይደርሳል፡፡ በመደበኛነት ከምንሰራቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት ውጪ ባለፉት ጥቂት ወራት እነዚህን ቁልፍ የሆኑ ስራዎች አከናውነናል፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ቁጥር እያደገ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ከዚህጋርተያይዞየሚታየውን የቤተ መጻህፍቱን መጨናነቅ ለመቅረፍ ምን እቅድ አላቸሁ?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፡-** እንደተባለው የተማሪ ቁጥር እየጨመረ ሄዷል፡፡ በዚህም ምክንያት ሁለቱም አብያተ መጻሕፍት ይጨናነቃሉ፡፡ ተማሪውም በዓመቱ መጀመሪያ በሚሰጠው ኦርየንቴሽን አማካይነትም ስለቤተ መጻሕፍቱ አጠቃላይ ግንዛቤው ስለሚኖረውና በሂደትም የሚሰጠውን አገልግሎት ሲመለከት የመጠቀም ፍላጎቱ ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ በዚህ የተነሳ ቤተ መጻሕፍቱን የሚጠቀመው ተገልጋይ ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ለበላይ ኃላፊዎች አቅርበን የበላይ ኃላፊዎችም ፈጣን የሆነ ምላሽ ሰጥተው ከቤተ መጻሕፍቱ ጀርባ ያለውን ስፍራ ላይ ከዋናው ቤተ መጽሐፍ ጋር ተያያዥ የሆነ አስር ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ህንጻ እንዲሰራ ተፈቅዷል፡፡ ከዚህም ባሻገር የዲዛይን ስራውን ከያዘው አካል ጋር በመሆን የእኛን ፍላጎት በዲዛይኑ ለማካተት የምክክር ስራዎችን ተሰርተዋል፡፡ በዲዛይኑም የጎደለንን ነገር ለምሳሌ የአካዳሚክ ስታፍ የማንበቢያ ስፍራና የመሳሰሉትን ያካተተ ሶስት መቶ ሰዎችን የሚያስተናግድ የጸጥታ ማንበቢያ ስፍራ ለማድረግ ነው ያቀድነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ዲዛይኑ ተሰርቶ ወደጨረታ ሂደት ተሻግረናል፡፡ ኮንትራክተሮቹ ከተለዩ በዚህ ዓመት ወደስራ ይገባል ማለት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የበላይ አመራሩ የወሰደው አፋጣኝ ውሳኔ የሚያስመሰግነው ነው፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- በቤተ መጻህፍቱ ያለው የመጻህፍት ክምችት ምን ይመስላል?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፡-** ባለፈው ክረምት ባደረግነው ቆጠራ በቤተ መጽሐፉ ሰላሳ አምስት ሺ የሚሆን የመጽሐፍ ክምችት መኖሩን አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሰላሳ አምስት ሺ ኤሌክትሮኒክ ሬሶርሶች በሰርቨር ላይ ይገኛሉ፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- የዲጂታል ላይብራሪስ ምን ይመስላል?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፡-** የዲጂታል ላይብረሪው ዩኒቨርሲቲው ሊኮራበት የሚገባ ትልቅ ስራ የተሰራበት ላይብራሪ ነው፡፡ ቀደም ሲል የነበሩት



ባለሙያዎችም ሰፋት ዌሩን ፈጥሮ እዚያም ላይ ዲጂታል ላይብራሪውን በማበልጸግና መጻሕፍቱን ወደቋቱ በማስገባት ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ ስራ ሰርተዋል፡፡ ባለፉት ጥቂት ወራትም ሁለት ባለሙያዎች እነዚህን ከአምስት ሺ በላይ መጻሕፍት ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ወደቋቱ አስገብተዋል፡፡ በአጠቃላይ የዲጂታል ላይብራሪው ቡድን የዩኒቨርሲቲውን ቤተ መጻሕፍት ለማሳደግ የሚያደርጉት ስራ በጣም የሚደነቅ ነው፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ከሎች ተመሳሳይ የትምህርት ተቋማት ጋር ያላችሁ ትስስር እና ትብብር እንዴት ይገለጻል?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፡-** ከሌሎች አብያተ መጻሕፍት ጋር ተገልጋዮች ከእኛ ዘንድ የማያገኙትን አገልግሎት ሌሎች ተቋማት ጋር በመሄድ እንዲጠቀሙ ለማድረግ የሚያስችል የትብብር ስርዓት አለን፡፡ ተገልጋዮች ይህንን ስለማይጠይቁ እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት ወይም ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመሄድ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል፡፡


በሌላ በኩል “የኢትዮጵያ አካዳሚክና ምርምር ላይብራሪ ኮንሰርን ቲም” የሚባል ማህበር አለ፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የአካዳሚክ አብያተ መጻሕፍት ማህበር ነው፡፡ በዚህ ማህበር አማካይነት የልምድ ልውውጦችን የማድረግ፣ ያሉ ግብዐቶችን የመጋራት ፣ በጋራ የኤሌክትሮኒክ ማቴሪያሎችን የመግዛትና የመሳሰሉት ስምምነቶች አሉን፡፡ ለምሳሌ ለአንድ ዳታ ቤዝ ሃያ አምስት ሺ ዶላር ቢጠይቅ ያሉት አብያተ መጻሕፍት በጋራ አዋጥተው ለመግዛት ያስችላል፡፡ በማህበሩ አማካይነት ስልጠና ሲኖር የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች እንዲሳተፉም ይደረጋል፡፡ ከዚህ ማህበር ብዙ ነገሮችን እንጠቀማለን፡፡ ከብሔራዊ ቤተ መዛግብት ጋርም ጠንካራ የሆነ ትብብር አለን፡፡ በሚያዘጋጇቸው ወርክሾፖችና ስልጠናዎች ላይም እንድንሳተፍ ይጋብዙናል፡፡ በቅርቡም ለሰራተኞቻችን ስልጠናለመስጠት ዕቅድ ተይዟል፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ከተቋሙ ተማሪዎችና ሰራተኞች ሌላ ያላችሁ ደንበኞች እነማን ናቸው?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፡-** ቤተ መጻሕፉን ለመጠቀም የሚመጡ በርካታ የውጪ ተገልጋዮች አሉን፡፡ በአካባቢው ጥሩ የሚባል ቤተ መጻሕፍት ባለመኖሩ የተነሳ በርካታ የማስተርና የፒኤች ዲ እንዲሁም የፖስት ዶክቶራል ተመራማሪዎች የህክምና ተማሪዎች ጭምር ቤተ መጽሐፉን ለመጠቀም ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን ካለን የቦታ ጥበት አንጻር ቅድሚያውን የምንሰጠው ለተማሪዎቻችን በመሆኑ በፈተና ወቅት አናስተናድጋቸውም፡፡ ከፈተና ወቅት ውጪ ባለው ጊዜ ግን የተወሰኑት የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የማስተርስ እና የፒኤች ዲ ተማሪዎች ደብዳቤ እንዲያመጡ በማድረግ የሁለትና የሶስት ወር የንባብ አገልግሎት እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለዓመት አምስት መቶ ብር እንዲከፍሉ በማድረግ አገልግሎቱን እንዲያገኙ የምናደርግበት ሁኔታም አለ፡፡ እኛ ባለብን የቦታ ጥበት ምክንያት ገድበነው እንጂ ከአካባቢው ማህበረሰብ የሚመጣው ጥያቄ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ፡- ቤተ መጽሐፉ ገቢን ከማመንጨት አንጻር በምን መልኩ እየተንቀሳቀሰ ነው? ምን ያህል ገቢስ አመንጭቷል?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ፡-** ቤተ መጽሐፉ ቀድሞም ገቢ ያመነጭ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በዋጋ ባይተመንም ቀደም ሲል ዲጂታል ላይብረሪው ሃያ ዘጠኝ ሺ ኤሌክትሮኒክስ ሪሶርስ ነበረው፡፡ ባለፉት ሰባት ወራት ደግሞ 7837390.38 ብር የሚተመን ሪሶርስ አደራጅቷል፡፡ ይህ በራሱ አንድ ገቢ የማመንጨት ተግባር ነው፡፡ በዚሁ ስለሚቀጥል በዓመቱ መጨረሻ ላይ ከፍተኛ ዋጋ ነው የሚኖረው፡፡ በሌላ በኩል ካየነው ደግሞ ይህ ስብስብ ዩኒቨርሲቲውን ከብዙ ወጪ የሚያድነን ነው፡፡ በዓመቱ መጀመሪያ እንዲገዙ የጠየቅናቸው መጻሕፍት እስካሁን በግዢ ሂደት ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መጻሕፍት ወደሃምሳ በመቶ የሚሆኑትን ግን በሶፍት ኮፒ በመልቀም በሰርቨር ላይ እንዲጫኑ አድርገናል፡፡ በዋጋ ስንተምናቸው ወደ ሶስት ሚሊዮን ብር ይሆናል፡፡ ይህ በራሱ እንደ ሌላ




ገቢ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ከዚህ ሌላም ምንም እንኳን እንደ ገቢ ምንጭ ሳይሆን እንደ ማህበረሰብ አገልግሎት የምናየው ቢሆንም ከውጪ ተገልጋዮች የሚገኝ የተወሰነ ገቢ ይኖራል።

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- ለወደፊትስ ምን ምን ነገሮችን ለመስራት አቅዳችኋል?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ:-** በረጅም ጊዜ ከያዝናቸው ዕቅዶች መካከል አሁን በቤተ መጽሐፉ እየተሰራ ያለው ስራ ከሌሎች የትምህርት ተቋማት እና ከተቀመጠው ስታንደርድ አንጻር ደረጃውን የጠበቀ ነው ወይ የሚለውን ለመፈተሽ ይረዳን ዘንድ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለመስራት እናስባለን ። የቤተ መጻሕፍቱን አደረጃጀትም በማጥናት ደረጃውን የጠበቀ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት እንዲሆን እንሰራለን። ስለዚህ እንደ ማንኛውም ኢኒስቲትዩት አደረጃጀቱን፣ ስታፉን፣ ኃላፊነቱን ወዘተ. በተመለከተ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሌጅስሌሽን ውስጥ ቤተ መጽሐፉም የራሱ የሆነ ክፍል (ቻፕተር) እንዲኖረው ለማድረግ እንሰራለን። በየኮሌጆቹ ቅርንጫፍ ቤተ መጻሕፍትን ለማስፋፋትም የምንሰራ ይሆናል። ቤተ መጻሕፍቱን ለማዘመን በምናደርገው እንቅስቃሴ ኤሌክትኖኒክ ሪሶርሶች ላይ አመዝነን እንሰራለን ፡ ፡ የመረጃ ምንጮችን በተመለከተም ያለ ማቋረጥ ግዢ የምንፈጽም ይሆናል። እንደ አካዳሚክ ተቋምነታችን ከአምስት ዓመት በላይ ያሉ መረጃዎች ያረጁ ስለሚሆኑ በተቻለ መጠን የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማቅረብ እንሰራለን። የምናቀርባቸው ፋሲሊቲዎችም ለተጠቃሚዎች ምቹ እንዲሆኑና በቅርብ እንዲገኙ ለማመቻቸት እንሰራለን። በቤተ መጽሐፉ ከበር ጀምሮ ያሉትን ስራዎች በሙሉ ኦቶሜት ለማድረግ፣ ኤሌክትሮኒክ የሆነና የዘመነ አሰራርን ለመከተል፤ ጥበቃውንም በሴኩሪቲ ካሜራ የተደገፈ ለማድረግ ሁሉ እናስባለን።

የሰው ኃይሉም በዕውቀት እና ክህሎት ራሱን እንዲገነባ የተለያዩ ስራዎች ይሰራሉ። የዩኒቨርሲቲው አጋር ከሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ቤተ መጽሐፉን ሊያግዝ ከሚችል ኢንተርናሽናል ተቋም ጋር ትብብር እንዲኖረን እንፈልጋለን። ከዚህ የተነሳም ከእህት ተቋማት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እንሰራለን። በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ዘንድም የንባብ ባህል እንዲያድግ አውደ ጥናትና አውደ ርዕይ ለማዘጋጀት ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ዕቅድ ይዘናል። በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም የንባብ ባህል እንዲያድግ ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት ስላለን የንባብ ባህልን ለማሳደግ እንሰራለን።

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- በመጨረሻ የሚሉት ነገር ካለ?***

**ወ/ሮ አመለወርቅ:-** በቤተ መጻሕፍቱ እስካሁን ለተሰሩት ስራዎችም የብዙ ሰዎች አሻራ አለበት። የበላይ ኃላፊዎችም ቤተ መጻሕፍቱን ለማደራጀትና ለማገዝ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት ነው ያላቸው። ይህን ባህል እንዲቀጥሉበት አደራ ለማለት እወዳለሁ፡ ፡ የቤተ መጻሕፍቱ ሰራተኞችም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው የሚደነቅ ስራዎች ሲያከናውኑ ቆይተዋል። እነዚህ ሁሉ ስራዎችም የተሰሩት ጥሩ የቡድን ስራ መንፈስ በመኖሩ ነው። እናም የእነርሱን ስራም ሊመሰገን ይገባዋል። የሌሎች የስራ ክፍሎች እንደ ጠቅላላ አገልግሎት ፣ ቴክኒክ ክፍል እና ሌሎችም በሙሉ ድምር ውጤት ነው የቤተ መጻሕፍቱ ስኬት። በመሆኑም ሁሉም የስራ ክፍሎች ለቤተ መጻሕፍቱ በማበርከት ላይ ያሉትን አስተዋጽኦ የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማሳሰብ እወዳለሁ።የዩኒቨርሰቲው ማህበረሰብም በቤተ መጻሕፍቱ ብዙ ስራዎች እየተሰሩ በመሆኑ መጥተው እንዲጠቀሙ እና የጎደለውንም ነገር በመመልከት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አደራ ለማለት እወዳለሁ።

***ዓ/አ/ህ/ግ/ማ/ዳ:- ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ከእኛ ጋር ላደረጉት ሰፊ ቃለ ምልልስ ከልብ እናመሰግናለን።***

**ወ/ሮ አመለወርቅ:-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የአረንጓዴ ክለብ ምስረታ በኢ.ሲ.ሰ.ዩ

የሰው ልጅ ከአካባቢውም ሆነ ከከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶችን ወደሚፈልገው ቅርጽና ውጤት በመለወጥ ለራሱ ጥቅም በማዋል ለዘመናት ሲጠቀም ቆይቷል፡፡ ይሁንና እንደየማህበረሰቦች የዕድገት ደረጃና የፍላጎት መጠን ማደግ እንዲሁም ዘመን የወለዳቸው ቴክኖሎጂና ስልጣኔ አስገዳጅነት የተነሳ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውና የአኗኗር ዘይቤው በአካባቢው ላይ እያደረሰው ያለው ተጽእኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ በመሄዱ በአሁኑ ወቅት አስከፊ ከሚባል ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ይህን ተከትሎም የዓለም ህዝብ ቀደም ሲል በቸልተኝነት፣ በራስ ወዳድነትና በስግብግብነት እንዲሁም ከንቃተ ህሊና ማነስ ያጠፋውንና ያደረሰውን የአካባቢ ብክለት ለማስተካከልና ለማረም ብሎም ስነምህዳሩን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ያላሰለሰ ጥረት ለማድረግ በመሯሯጥ ላይ ይገኛል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም በምትከተለው የአረንጓዴ ልማት መርህ በቀጣይ ዓመታት ዕቅዷ ውስጥ የአካባቢ ጉዳይን በማካተት እየሰራች እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ የሀገሪቷ ዕቅድ ውጤታማ የሚሆነው ደግሞ መላው የህብረተሰብ ክፍል የየራሱን ድርሻ በአግባቡ ሲወጣ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ለዚህ ዕቅድ መሳካት ተቋማትና በውስጣቸው የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በቅንጅት መንቀሳቀስ በአካባቢ ጉዳዮች ላይ የሚታየውን ችግር ለመፍታት የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስድ ይታመናል፡፡




ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲም የአካባቢ ጉዳዮች ላይ በተለያየ መልኩ እንደሚሰራ የሚታወቅ ነው፡፡ በትምህርት ፕሮግራሙ ከአካባቢ ጋር የተያያዙ የትምህርት መስኮችን በመክፈት፤ በስልጠና፣ በማማከር፣ እንዲሁም በምርምርምና የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፉም ከአካባቢያዊና አየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በርካታ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ስራዎች በተቀናጀ መልኩ ሳይሆን በተለያዩ የስራ ክፍሎች አማካይነት ሲከወኑ የቆዩ በመሆናቸው፤ ዩኒቨርሲቲው በዕለት ተዕለት ተግባራዊ እንቅስቃሴው ውስጥም የአካባቢ ጉዳዮችን በስፋት አካቶ በተቀናጀ መልኩ ለማስኬድ ብሎም ዩኒቨርሲቲው ማህበራዊ ኃላፊነቱን በላቀ ሁኔታ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በዩኒቨርሲቲው የ "አረንጓዴ ክለብ" በቅርቡ ተመስርቷል፡፡ ይህ ክለብ የዩኒቨርስቲው ከፍተኛ አመራሮችን ጭምር ያካተተ ሲሆን የሚመራውም በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደት

ሰብሳቢነትና በስልጠናና ማማከር ዘርፍ ምክትል ፕሬዚደንት ምክትል ሰብሳቢነት ነው፡፡ በከፍተኛው የዩኒቨርሲቲ አመራር ትኩረት አግኝቶ መመስረቱም ወደፊት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ስኬትና ውጤታማነት የራሱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ዩኒቨርሲቲው እንደከፍተኛ የትምህርት ተቋምነቱ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራም አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ክለቡ የተቋቋመብትን አላማና የሚያከናውናቸውን ተግባራት አስመልክቶ ዶ/ር አዜብ አሰፋ የባለ ብዙ ዘርፍ የስልጠናና ማማከር ማዕከል አማካሪ ተጠይቀው ሲያብራሩ ሀገሪቱ የምታካሂደው የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲ መሆኑን አስታውሰው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲም እንደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በአካባቢ ጉዳዮች ላይ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ የራሱን ግዴታ መወጣት እና ማህበረሰቡ ብሎም ሀገሪቱ ከአካባቢ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የራሱን አስተዋጽኦ ለማበርከት በማሰብ የተቋቋመ ክለብ መሆኑን በመግለጽ በዩኒቨርሲው ውስጥ በተለያየና በተበታተነ ሁኔታ የሚሰሩትን ስራዎች መዋቅራዊና ዘለቄታዊነት ባለው መልክ ለማከናወን የሚሰራ ክለብ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከአካባቢ ጉዳይ ጋር ተያይዞ በዩኒቨርሲቲው በርካታ ስራዎች እንደሚሰሩ የጠቀሱት ዶ/ር አዜብ እነዚህን ስራዎች ሲዘረዝሩ በትምህርት ዘርፉ እና በስልጠናና ማማከሩ ዘርፍም የሚሰሩ ስራዎች እንዳሉ ሆነው የዩኒቨርሲቲውን ምድረ ግቢ አረንጓዴ የማድረግ ስራም እየተሰራ መሆኑንና ዩኒቨርስቲውን አቋርጦ የሚያልፈውን ወንዝ ለማልማት ፕሮፖዛል የተቀረጸ መሆኑን ጠቁመው ምድረ ግቢውን ማስተካከልና በመሳሰሉት ጉዳዮችም ላይ በተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት የሚሰሩ ስራዎች መኖራቸውን አስረድተዋል፡ ፡ ወደፊትም በዩኒቨርሲቲው ግቢና በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ትኩረት አድርጎ የአረንጓዴ ልማት የማካሄድ ስራን እንደሚያከናውን የገለጹት ዶ/ር አዜብ ከእነዚህ መካከል አንዱ አከባቢያዊ ሁኔታቸው አንጻር በመመርመር ተክሎችን እየመረጠ ግቢውን አረንጓዴ ማድረግ የሚለው ላይ በስፋት እንደሚሰራበት ገልጸዋል፡፡ የአካባቢ ጉዳይ አንድ አካልና የተወሰነ አካባቢን ብቻ የሚመለከት ባለመሆኑ የአካባቢውን ማህበረሰብም በማሳተፍ የአካባቢ ልማትን ለማካሄድ ክለቡ እንደሚሰራም አስረድተዋል፡፡

ይህ አረንጓዴ ክለብ የዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች በየዕለቱ በሚያከናውኗቸው ተግባራት የአካባቢ ጉዳይን ከግምት ውስጥ አስገብተው ለመስራት እና የአካባቢ ጉዳይ እንዴት ነው ሊካተት የሚችለው የሚለውን በመጠየቅ ስትራቴጂ በመንደፍ ለመንቀሳቀስ የሚያስችልም ክለብ ነው፡፡ ለአብነት ያህልዩኒቨርሰቲውየተለያዩግብዐቶችናአገልግሎቶችን ይጠቀማል፤ ከየስራ ክፍሎች የሚወጣ ተረፈ ምርት ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የሆነ የወረቀት ፍጆታ አለ፡፡ ይህ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የወረቀት ተረፈ ምርት እንዲኖር ያስገድዳል፡፡ ይህን ከአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ተጣምሮ ሲታይ የሚኖረውን ተጽእኖ ቀላል የሚባል ባለመሆኑ ብክለትንም ሆነ ብክነት ለመቀነስ ግንኙነቶችን ከወረቀት በጸዳ መልኩ በኢሜል መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ በኢኮኖሚውም ሆነ በአካባቢ ጥበቃ ረገድ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ክለቡ በግቢው ማህበረሰብም ሆነ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ግንዛቤን ለመፍጠር ይሰራል፡፡ የምንጠቀምባቸውን ግብዐቶች በጠቅላላው በአካባቢያዊ ሁኔታው ላይ የሚያመጣውን ተጽእኖ አስቀድሞ በመገንዘብ በአግባቡ ለመጠቀም ግንዛቤን የማሳደግ ሁኔታ ላይ ይሰራል፡፡



በየዕለቱ እንቅስቃሴዎቻችን የምንፈጥራቸው አካባቢያችን ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን ለመቀነስ ይንቀሳቀሳል። ለዚህም እንደየደረጃቸው ቅደም ተከተል ተዘጋጅቶ በምድረ ግቢው፣ በቆሻሻ አወጋገድ፣ የአካባቢ ማገገም እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙርያ በርካታ ስራዎች በክለቡ አማካይነት የሚሰሩ ይሆናል።

ክለቡም ለስራው ያመች ዘንድ በቅድሚያ የአካባቢ ኦዲት በማድረግ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ደረጃ ይለያል። በመቀጠልም በየትኛው ረገድ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ በመለየት “የትኛውን ተረፈ ምርት መቀነስ እንችላለን? የትኛውን ደግሞ እንደገና እንጠቀማለን? የትኛውንስ በተገቢ ሁኔታ እናስወግደዋለን?” የሚለውን ለመለየት አካባቢያዊ ኦዲት በማካሄድ የግቢውን እና የአካባቢውን ሁኔታ መገምገም እና ከዚያ በመቀጠል ዝርዝር ተግባራትንና ግቦችን በማስቀመጥ የሚሰራ መሆኑን ከዶ/ር አዜብ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል። በሌላ በኩል ሲታይ የአካባቢ ጉዳይ ሁሉንም የህበረተሰብ ክፍል ተሳትፎ የሚጠይቅ ጉዳይ በመሆኑና በጥቂት ኮሚቴ አባላት ብቻ የክለቡን አላማ ለማሳካት የሚታሰብ ባለመሆኑ በጎ ፈቃደኛ ተማሪዎችንና የዩኒቨርስቲው ሰራተኞችን በማሰባሰብ የበጎ ፈቃደኞች ክለብ ለማቋቋም እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

ከዩኒቨርሲቲው ሰራተኞችና ተማሪዎች የሚወጣጣው ይህ የበጎ ፈቃደኞች ክለብ አማካይነት በተግባር የሚሰሩ ስራዎችንም ሆነ የምሁራን አስተያየት የመሳሰሉትን በማሰባሰብ ህብረተሰቡ ጋር ተደረራሽ የሆነ ስራን ለመስራት እንዲሁም በተለያዩ አካላት አማካይነት እየተሰሩ ያሉ የአካባቢ ጉዳዮችን መዋቅራዊ በሆነ መንገድ ተቀናጅተው እንዲሰሩ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይታሰባል።

የአከባቢ ጉዳይ በሀገራችን እንደቅንጦት ሲታይ ቆይቷል። የሁሉም ዜጋ ጉዳይም ተደርጎ አይታሰብም፡ ፡ ነገር ግን የአካባቢ ጉዳይ የቅንጦት ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአካባቢያዊ ችግር በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል ። ለዚህ ችግር መፍትሔ የሚመጣው እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል የሚያደርገው አነስተኛ ናቸው ተብለው የሚገመቱ ተግባራት በሚያመጡት የጋራ ድምር ውጤት ነው። ስለዚህ ሁሉም ሰው “ የአካባቢ ጉዳይ ያገባኛል፤ ይመለከተኛል። የእኔ አስተዋጽኦ ተደምሮ ነገ ትልቅ ውጤት ይኖረዋል።” ብሎ በማሰብ መንቀሳቀስ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል የአካባቢ ጉዳይ ብዙ መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቅ ጉዳይም ተደርጎ ይወሰዳል። በግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚደረጉት እንዳሉ ሆነው በአመለካከት ለውጥ ብቻ የሚሰሩ በርካታ ተግባራትም ይኖራሉ፡ ፡ የአረንጓዴ ልማት ለማካሄድ ሀገሪቷ የነደፈችው ዕቅድ የሚሳካውም እያንዳንዱ ዜጋ የየራሱን ድርሻ በአግባቡ ተገንዝቦ የበኩሉን ሲወጣ ነው። ለዛሬ ብቻም ሳይሆን ለሚመጣው ትውልድም የጸዳ አካባቢን ማስረከብ የሚለውንም ማሰብ ተገቢ ይሆናል። “ረጅም ርቀት በአንድ እርምጃ ይጀመራል” እንዲሉ አበው ታላላቅ ነገሮችን ለማከናወን መነሻው ከትንሽ መጀመር በመሆኑ በዚህም ዩኒቨርሲቲው በሚካሄደው የዚህ ጽዱና አረንጓዴ አካባቢ እንዲኖር የመስራት ተግባር ከዩኒቨርሲቲው ግቢ በመጀመር ወደ አካባቢያዊ ብሎም ወደ ከተማ አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ ታቅዷል። በዚህ ክለብ ውስጥ በመሳተፍ በየአካባቢው እየተተባበሰ የመጣውን ይህን ችግር ለመቅረፍ እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጥረትና ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ለዚህም ሁሉም የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በዚህ የበጎ ፈቃድ አባልነት ላይ ተሳትፈው ዩኒቨርሲቲያችን ያለበትን ማህበራዊ ኃላፊነት እንዲወጣ፤ ለአካባቢው ማህበረሰቡ ደግሞ ምቹ እና አረንጓዴ በሆነ አካባቢ ውስጥ መስራትን አንዱ አላማችን አድርገን የሚጠበቅብንን ሀገራዊ ኃላፊነትን መወጣት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የበጎ ፈቃደኞች አረንጓዴ ክለብ ብዙ መስፈርቶችን የሚጠይቅ ሳይሆን ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚሳተፍበት ክለብ ነው።

ስለዚህ ማንኛውም ሀገር ወዳድ የሆነ ዜጋና የቀጣዩ ትውልድ ህልውና የሚያሳስበው አካል ሁሉ በዚህ የአረንጓዴ ክለብ ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት በመሳተፍ ክለቡ ለተቋሙ ብሎም ለሀገሪቱ ለማበርከት ያለመው ታላቅ ዓላማ ህልው ይሆን ዘንድ የድርሻውን እንዲወጣ ከአደራ ጭምር ለማሳሰብ እንወዳለን።

**“ ጽዱና አረንጓዴ ዩኒቨርሲቲ እና አካባቢ የመፍጠር ኃላፊነት አለብን!”**

# International and Public Relations Coordination Directorate

Tel.0116 46 2887 Extension: 253/252/257 Fax: 0116463016 P.O.Box5648
E-mail: www.Ipro @ecsu.edu.et : Pr.ecsu@gmail.com Website: www.ecsu.edu.et Tweeter: @ECSU tweets
FM Radio:-100.5MHz Facebook: Ethiopian Civil Service University

ተገልጋይ ተኮር

ሁሌም መማር

Continuous Learning

ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

Customer Focus

Commitment

ቁርጠኝነት

Ethiopian Civil Service University

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

ECSU

Est. 1995

BUILDING CAPACITIES IN THE PUBLIC SECTOR

Collaboration

አሳታፊነት

ትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከር፣ በምርምር



የመምህራን እና የሰራተኞች መኖሪያ



የመኖሪያ ህንፃ



የሰልጣኞች ዶርሞተሪ

አዳዲስ የሚሰሩ የግንባታ ፕሮጀክቶች



አካዳሚክ ህንፃ



የወሊሶ ህንፃ

